
# መቃብር አፋፍ ላይ ሆኖ ቅጥፈት፡ የስብሓት (ወልደ-ሥላሴ) ነጋ ያመረረ ፀረ-ኢትዮጵያ እና ፀረ-ህዝብ አቋም በተለያዩ ቃለ-ምልልሶች አሥረጂነት

ከሰሎሞን ወልደ-አብ

**“[በቅድመ - ተ.ሓ.ህ.ት. ኢትዮጵያ ኢትዮጵያዊያን] አንድ አልነበርንም ፤ አንተዋወቅም። አንተዋወቅም፤ አንተዋወቅም። ስንተዋወቅ አልነበርንም ”**

**ስብሓት (ወልደ-ሥላሴ) ነጋ**





በቅርቡ የተጋድሎ ሓርነት ህዝቢ ትግራይ (ተ.ሓ.ህ.ት.) አመራር አባል የሆኑት አቶ ስብሓት ነጋ (ወልደ-ሥላሴ ነጋ)[i] ከአሜሪካን ድምጽ ራድዮ የአማርኛው ክፍል ጋር ቃለ-ምልልስ አድርገው ነበር። በዚሁ ቃለ-ምልልስ አቶ ስብሓት ያን ያሰለቸንን ፀረ-የኢትዮጵያ ታሪክና አንድነት አቋማቸውን አበክረው አንጸባርቀዋል። ይህን ያህል ጊዜ የአገሪቱ የሥልጣን ኮርቻ ላይ ከከረሙና የአገሪቱን ጓዳና ጉድጓድ ጐልጉለው ካወቁ በኋላም እንዴት ሊያስተውሉ፣ ሊማሩና ጥላቻው በርዶላቸው ሊቀየሩ እንዳልቻሉ ፈጽሞ ሊገባኝ አልቻለም። ይህ አቋማቸው የፈጠረብኝ **ግራሞት** ገፋፍቶኝ ቀደምት ቃለ-ምልልሶቻቸውና ንግግሮቻቸው ፍለጋ ገባሁ፤ ለማነፃጸር ያህል ብዬ። ከቃለ-ምልልሱ ሌላ ያገኟቸው ውጤቶች ደግሞ በጣም ለማመን የሚከብዱና በጣምም የሚያሳዝኑ ነበሩ። ከነዚህ ትኩረቴን ከሳቡት የሰውዬው ዲስኩሮች መካከል የአክሱም ስርወ - መንግሥት ዓጋመንና ተምቤንን እንደማያካትት አስመልክቶ የተናገሩትና[1] ”እንደርታዎች[ii] ትልቅ አምባሻ (ዳቦ) እንጂ ትልቅ ሰው የላቸውም (እንደርታ ዓብዩ ሕምባሻ እምበር ዓብዩ ሰብ የብሎምን)”[2] ያሉት ይገኙባቸዋል። አባባሎቹ ባዶዎች፣ ኃላፊነት የጎደላቸውና ፀረ-ህዝብ አቋም የሚያንጸባርቁ ናቸው። ከዚህ በላይ ደግሞ እነዚህ የሰውዬው እምነቶች ፀረ አንድነት ባህሪያ ያላቸውና በጭፍን ጥላቻ ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው በጣም የሚሳዝኑም የሚያናድዱም ናቸው። እንዲህ ዓይነት መረን የለቀቀ ዋልጌነት፣ ህዝብን መዘርጠጥና የታሪክ ክህደት በቸልታ ሊታለፍ አይገባም ብዬ አምናለሁ። ጊዜው ፈቃጅ ሆኖ ባለመገኘቱ ተገቢው ቅጣት ባያሰጣቸውም ተገቢው መልስ ግን ሊያገኙበት ይገባል። በቀሩት ሁለት ጉዳዮች ላይ ወደፊት የምመለስባቸው ስሆን ለጊዜው ግን መነሻየ በሆነው በቃለ-ምልልሱ ላይ ማተኮርን መርጫለሁ። ወደ ዝርዝር አስተያየቴ ከመግባቴ በፊት ግን እንዲታወቅ የምፈልገው አንድ ነጥብ አለ። በቃለ-ምልልሱ ወቅት ጠያቂዎቹ አቶ ስብሓትን ከቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ. ቆርቋሪዎች አንዱና አንጋፋ እንዲሁም የቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ ፈጣሪ በማለት ገልጸዋቸዋል። የአቶ መለስ መታመምን አስመልቶ ጥያቄ ያቀርበላቸው የአሜሪካን ድምጽ ሬድዮ ጋዜጠኛም መሰል አገላለጽ ተጠቅሟል። በሌሎች ዘንድም ይህ አባባል ሲደጋገም ይሰማል ወይም ይታያል። ስለ አቶ መለስ (ለገሰ) ዜናዊም እንደዚህ የመሳሰሉ አባባሎች ይሰነዘራሉ። ይህም አንዳንዶቹ በየዋህነትና ካለማወቅ ሲያደርጉት፤ ሌሎቹ ደግሞ ሰዎቹን የበለጠ ለመካብ ከመነጨ ፍላጎት የሚፈጽሙት ጉዳይ ነው። ያም ሆነ ይህ መረጃው ስህተት ነው፤ ሁለቱም ቆይተው የተቀላቀሉ እንጂ መስራቾች አይደሉም።[3] በነገራችን ላይ ክቡር አለማለቴ ገዢዎቻችን ክቡር፣ የተከበሩ ምንትስ እየተባባሉ እርስ በራሳቸው እንደሚመጻደቁት ሳይሆን ሰው ሁሉ ክቡር ነው፤ በግብሩ ራሱን እስካላረከሰ ድረስ ብየ ስለማምን ነው።

---

1 ስብሓት ነጋ (2004)

2 ስብሓት ነጋ (?)

3 Berhe, K. (2005:51); Berhe, A. (2009:62)

ወደ መነሻ ጉዳዬ ልመለስ። አቶ ስብሓት (ወልደ-ሥላሴ) ነጋ በቃለ-ምልልሳቸው አጽንኦት ሰጥተው ያሰመሩበት መልዕክት በቅድመ-ተ.ሓ.ህ.ት. ኢትዮጵያ ኢትዮጵያዊያን "*አንድ አልነበርንም፤ አንተዋወቅም። አንተዋወቅም፤ አንተዋወቅም። ስንተዋወቅ አልነበርንም።*" የሚል ነበር። ግለሰቡ ይህንን አቋማቸውን ሲያብራሩ "ስንዋጋ ነበርን'ኰ፤ እርስ-በራሳችን ስንጠፋፋ ነበርን'ኰ። [ኢ.ህኣዴግ] አገሪቱን አንድ አደረገ እንጂ አንድነት እኰ አልነበረንም። የአመለካከት ጉዳይ ነው። በታንክ አንድ ማድረግ፣ በጄት አንድ ማድረግ፣ በብረት አንድ ማድረግና በመፈቃቀርና በመተማመን በእኩልነት አንድ ማድረግ፤ የብሄር/ብሄረ-ሰቦች እኩልነትን ያረጋገጠ አንድነት። እና ይሄ ስንዋጋ፣ ስንተላለቅ የነበረው ይሄ ነበር እኰ ታሪካችን" ብለውናል።

በመቀጠልም አቶ ስብሓት የአሁንዋ ኢትዮጵያ በታሪክዋ ለመጀመሪያ ጊዜ አማራው ከትግሬው፣ ትግሬው ከሶማሌው ተፋቅሮ የሚኖርባት "በመንግሥት ላይ የተቆጣ ህዝብ የሌለበት ሥርዓት" የተገነባባት አገር ለመሆን መብቃትዋን ነግረውናል። እንዲህ ያለ ነገር ምን ሊባል ይቻላል?!የቀን ቅዠት? እብደት? ድንቁርና? የዋህነት?መጃጀት? እልህ? ወይስ ካፈርኩ አይመልሰኝ?ይህ የአገላለጽ ችግር ነው መሆን ያለበት። በእውነት ገዢዎቻችን ከልባቸው እንዲህ ያስባሉ ብሎ ማመን ይከብዳል። ይህን ያህል ይንቁናል እንድልል ደግሞ ሰቀጠጠኝ። ቁጣውን ወደተግባር የተረጐመ ህዝብ የለንም ለማለት ከሆነ ልክ ነው፤ እኔም እስማማለሁ። የአገሪቱ ህዝብ ቁጣውን አምቆ እየቆዘመ ጊዜ የሚጠብቅ በመሆኑ መቆጣቱ አይታይም። ቁጣው በግላጭ ስለማይታይ ደግሞ አሌ ለማለትና እንዲያ አድርጐ ለማቅረብ ይመቻል። በበኩሌ እነ አቶ ስብሓት ይህንን አጥተዉት ነው ለማለት አይዳዳኝም፤ ለማንም የሚሰወር ነገር አይደለምና። ደግሞም እኰ እየጣሩና ሌት ተቀን እየደከሙለት ያለው የዕቅዳቸው ሁሉ አልፋና ኦሜጋ ነው። አቶ ስብሓት ክስተቱ በመዘግየቱ ቅር ተሰኝተው፣ ሳያዩት ጥርግ እንዳይሉ ሰግተው ከሆነ እረዳቸዋለሁ። ዕድሜያቸውን ሙሉ **የለፋለት** ነገር ግቡን መትቶ[4] ሳያዩ ማለፋቸው ቢያቃዣቸው በፍጹም ሊያስገርም አይገባም። ነውርም የለውም። ከዚህ ውጭ ግን የተናገሩት ነገር በሙሉ የእውነቱ ተቃራኒና መሠረት አልባ ቅዥበራ ነው። በምርጫ 97 ህዝቡ ያሳዬው አቋምና ያየነው እውነት የሚመሰክረው ይህንን ነው። ሙያተኛ አስተናጋጅ አጥቶ ለገዥዎቻችን ጥቃት ተዳረገና ተቀለበሰ እንጂ ቁጣማ እንዳለ እኛም ገዥዎቻችንም በዓይናችን በብረቱ አይተናል። ኢ.ህኣዴግ ዴሞክራሲ ብሎ ነገር ዳግም አይደገመኝም ብሎ በአደባባይ እንዲምል እንዲገዘት ያደረገው ህዝቡ ያሳዬው ቁጣ አልነበረም እንዴ? ቁጣ አለ፤ የሚያስፈራ፣ ቢፈነዳ ማጠፊያው የሚያስቸግር የተዳፈነ ቁጣ አለ።

አቶ ስብሓት ይመኑትም ይካዱትም ኢትዮጵያ የቆዳ ስፋትዋና የግዛት ክልልዋ እንደ ብዙዎች ሌሎች አገሮች ሲሰፋና ሲጠብ የኖረ ቢሆንም ዘመናት ያስቆጠረ ሥልጣኔና የመንግሥትነት ታሪክ ያላት አገር ናት። ይህ ደግሞ ያለ ሰዎች የተፈጸመ አይደለም። ይህንን የሰራ እየተፋቀረም እየተራኰተም አብሮ የኖረ **ህዝብ** አላት። አብሮ እየወደቀና እየተነሳ የገነባት **ህዝብ** በጋራ የሚኖርባት አገርም ነች። ህዝቧ የሚተዋወቅ ብቻም ሳይሆን በደም፣ በታሪክና በማንነትም የተሳሰረ ነው። ህዝቡ ይህንን ትስስሩን ጠላት ሲመጣ በጋራ እየመከተ የህይወት ዋጋ ጭምር ከፍሎ የፈጠረውና ጠብቆ ያቆየው ነው። የእነ አቶ ስብሓት አባቶች የዚህ ሂደት ተካፋይ አልነበሩ እንደሆነ ሌላ ጉዳይ ነው። በተቀረ ግን ይህ የአብዛኛው የአገራችን ህዝብ፤ የኤርትራ ህዝብም ጭምር፤ አያቶች፣ ቅድመ-አያቶች፣ ምንጅላቶች፣... የጋራ ገድል ውጤትና የጋራ ታሪክ ነው። የኢትዮጵያ የዘመናት ታሪክን የጡት ልጃቸው አቶ መለሰ (ለገሰ) ዜናዊም የአማራ ብሄር የገዥ መደቦችና ቡችላዎቻቸው የታሪክ ፀሐፊዎች ተረት-ተረት ብለው አጣጥለውት

4 Berhe, K. (2005); Berhe, A. (2009)

የነበረ ለመሆኑ የሚዘንጋ አይደለም።[5] ዛሬ ግን የአገርና የህዝብን ጠላት አሽቀንጥሬ አልጥልም ብሎ ለግሞ የተሸከማቸው መንበረ-ሥልጣን ላይ ለመሰንበት ብለውም ይሁን ልብ ገዝተው አላውቅም እያቀረሻቸውም ቢሆን የተቀበሉት ጉዳይ ነው። የሆነ ሁኖ ግን የትላንቱ የኢትዮጵያን ታሪክ የማንቋሸሽና ወደ መቶ ዓመት የማሽመድመድ ዲስኩር ዛሬ አይደመጥም። በተለይ ከባድሜ ግጭት በኋላ የኢትዮጵያ ታሪክ ወደሉሲ (ድንቅነሽ) ዕድሜ ተለጥጦ ተደስኩሮልናል። ከዚያ በፊት የኢትዮጵያ ታሪክ የሦስት ሺ ዓመት ዕድሜ ያስቆጠረ ነው ሲባል ሊያሳብዳቸው ይደርስ እንደነበረ ሁላችንም የምናውቀው ጉዳይ ነው። ከገዢዎቻችን ባህርይ ውስጥ በጣም የሚገርመው ይሉኝታ ቢስነታቸው ነው። የፈለጉትን ሲሉ ይከርሙና ተገልብጠው የዚህ ሲሉን የባጁትን ጉዳይ ተቃራኒ አቋም ይዘው ሲቀርቡ ምንም አይሰማቸውም። አዲሱ መልካቸው ይዘው ሲቀርቡ ያንን ትላንት ሲሉት የነበረውን ነገር እነርሱ ይሉት ነበር ብሎ ለማመን በጣም ያስቸግረኛል። ትግራይን ገንጥሎ ነፃ የማውጣትን አጀንዳ ወደ "ኢትዮጵያዊነት" አጀንዳ፣ ከአልባኒያ ኰሚኒስትነት ወደ ካፒታሊስትነት፣ ከሻዕቢያ ባለንጀራነት ወደ ሻዕቢያ ባላንጣነት (ባድሜ አካባቢ በ 1960 ዎቹ መጨረሻ ላይ ጀብሃን 'E.L.F.' በጋራ ወግተው ነበር።)፣ … መገለባበጥ ትንሽ እንኳን ማብራሪያ አያስፈልገውም? ይህ በሌሎች እርድና፣ ከሁኔታዎች ጋር ራስን ማዋሃድና መስተካከል ሊባል ይችላል፤ ለኔ ግን ይህ ራዕይ አልባነት ነው። ራዕይ የላቸውም። ራዕያቸው ሥልጣን ላይ መሰንበት ነው።

አቶ ስብሓት በቃለ ምልልሳቸው "*ሶማሊና ትግራይ የት ይተዋወቃል?አማራና አፋር የት ይተዋወቃል? አይተዋወቅም እኮ። ሊገዛ የሄደ ነው እንጂ አማራው ኢንቨስት አድርጐ በአፋር በሶማል አልታየም። …* [አሁን ግን] አንድነት የአንድነት ገመዱ እየተዘረጋ ነው።… እግዚአብሄር እንደፈጠርን ነው እኮ በክልላችን የነበርነው፤ *ፖሊስ መላክ፣ ወታደር መላክ፣ ጠቅላይ ገዢ መላክ* **[በቀር]**። አንድ አልነበርንም፤ አንተዋወቅም። አንተዋወቅም፤ አንተዋወቅም። ስንተዋወቅ አልነበርንም" በማለት አጽኖት ሰጥተው ሞግቷል። ይህ በሙሉ ስህተትም ውሸትም ነው። እስከ ምፅኣተ-ተ.ሓ.ህ.ት. ድረስ ኢትዮጵያ ኅብረ-ብሄራዊ አቋም በነበራቸው ሥርዓቶች ነበር የምትገዛው። ንጉሠ-ነገሥታዊም ሆኑ ወታደራዊ መንግሥታቱ ኅብረ-ብሄራዊ መንግሥታት ነበሩ። እነዚህ ገዥዎች የመደብ ወይም የፖለቲካ ጥቆሞቻቸው ለመጠበቅ ሁሉንም መንገድ ተጠቅመዋል። ጦር ተሰባብቀዋል፤ ክተት አውጀው ተወጋግተው አንዱ አንዱን አስገብረዋል፤ ተጠፋፍተዋል። ሻል ሲል ደግሞ ትሥሥራቸውን ለማደልደል በአምቻና ጋብቻ ጭምር እያጠናከሩ አካባቢያዊ ትስስሩን ሲያጠብቁት ኖረዋል፤ ይቅር-ይቅር ተባብለውም አብረው ኖረዋል። ህዝቡም ከማንም ተችሮለት ሳይሆን በገድሉና በደሙ አስከብሮ ባቆያት አንድ ባንዴራው ሥር ተጠልሎ በነፃነት በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች ሠርቶ ሲኖር ነበር። በዚያን ወቅት አገሪቱ **የጋራ ስለነበረች** ሌላ የተለያየ ባዕድ-ወለድ እራፊ ጨርቅ የሚያጣቅስበት ጐሳዊ የማንነት መለያ አላሻውም። በደሉም መከበሩም በጋራ ተካፍሎ ኖሮዋል።

የህዝብ ከቦታ ወደቦታ ተዘዋውሮ የመሥራትና የመኖር ሁኔታ በየጊዜው ከቴክኖሎጂ፣ ከመገናኛና ከህዝብ ብዛትና አሰፋፈር ዕድገት ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው። መቸም እንኳንስ ከዓድዋ ወደ መሃል አገርና ሌላው የአገሪቱ ክፍል ቀርቶ ከዓድዋ ወደ መቀሌ ለመጓዝ እንኳን ቀናት በሚወስድበትና ከፍተኛ ስንብት በሚጠይቅበት ዘመን የህዝብ ዝውውር እንደ አሁኑ ዘመን ሆኖ እንዲገኝ አይጠበቅም። የነገሥታቱ መልዕክት ለማድረስ ከመቀሌ ወደ አዲስ አበባ ወይም በግልባጩ ለሚላክ መልዕክተኛ ሳምንታት ይፈጅበት እንደነበር ወላጅ አባቴ አውግተውኛል። በዚያን ዘመን ከዘመድ አዝማድ ተለይቶ ርቆ መሰደድ ነውር፣ ብርቅ ወይም እርግማን ነበር። የመሬት ጥበት አልነበረም፣ የሰዉም ፍላጐት እንዳሁኑ ዘመን የተለጠጠ አልነበረም፤ መሬቱም ለጋስ ነበር። ከቀዬው በጣም ርቆ ስለሚገኘው አካባቢ

5 ህ.ወ.ሓ.ት (1979: 36-40).

የነበረው ዕውቀትም ውሱን ነበር። ርቆ የሄደውም ሁሉ የመመለስ ዕድሉ በበሽታ፣ በሽፍታም ሆነ በሌላ ችግር አሰናካይነት፣ በልብ ከአካል ጋር አብሮ መራቅ ወዘተረፈ ምክንያት አስተማማኝ አልነበረም። መሰደድ ከድህነት ጋርና ሠርቶ ንሮን ከማሻሻል እንጂ ንዋይን አፍሶ ሃብት ከማግበስበስ ጋር ቁርኝት አልነበረው። ድሃ እንጂ ያለው ሰው፣ ማዕዱ የሞላለት ሰው አይሰደድም ነበር። ይህ ሁሉ አካባቢህን ለቀህ የመሰደድን ፍልጐት ገዳቢና አምካይ ነበር።

**ከ 20 ኛው ክፍለ-ዘመን** መባቻ ጀምሮ ግን ሁኔታው ተቀይሯል። ይህ ግን ተ.ሓ.ሀ.ት./ኢ.ህ.ኣ.ዴ.ግ. የፈጠሩት ጉዳይ አይደለም። እነርሱ ተረት-ተረት ነው ወደሚሉት የጊዜ ክልል ሳንገባ ዘግየት ብለን ከአፄ ቴዎድሮስ ዘመን ጀምሮ ባለው ሁኔታ ላይ እንኳ ብንነጋገር ይህን እውነታ ማረጋጋጥ ይቻላል። ነገሥታቱ ግዛታቸውን ለማረጋገጥና የአመጸባቸውን መስፍን ወይም ንጉሥ ለማስገበር ሲዘምቱ እንደ ዘመናችን ሻንጣ ነትተውና ቦርሳ አንጠልጥለው ነጠላቸውን አይደለም። ወይም አምስትና አሥር አንጋች አስከትለው አልነበርም። በርካታ መሳፍንትና የዕምነት አባቶች **ኰልኩለው**፤ ሺና ሺ እግረኛና ፈረሰኛ ሠራዊት **አስከትተው**፤ ጋጋሪ፣ ወጥ-ቤት፣ ጠጅ-ጣይ፣ ጠላ ጠማቂ ከነሙሉ ድርጅታቸው **አስከትለው** ነበር የሚዘምቱት። ይህ ሁሉ ደግሞ እንዳለ ተመልሶ አይመጣም። አገር ጥሞት፣ ፍቅር እግር-ተውርች ጠፍንጐት፣ ቆስሎ ወይም ታሞ እስኪያገግም፣ ወዘተ የሚቀረውን መገመት ይገባል። አፄ ዮውሃንስ ወደ ጐጃምና ወደ ወሎ ያን ሁሉ ሰራዊት እያስከተሉ ሲዘምቱ ያስከተሉት ያሁላ ወጠምሻ ልቀም ብሎ ተመልሷል? እዚያ የቀረም የተዋለደም የለም? በምኒልክ ጊዜ አገር ሲቀና ወደ ደቡብ የዘመተው የሰላሌ ኦሮሞ እንዳለ ተመልሷል? ይህም ሠራዊት ዓለምን ክላልኝ ያለ መናኝ የባህታዊ ሠራዊት ነበርና እሱም አልወለደም አልተዋለደም? በአፄ ኃይለ-ሥላሴ ዘመን የነበረው ሠራዊትም እንዲያ ነበር? በደርግ ዘመን ከሁሉም የአገሪቱ ማዓዝናት ከትቶ ወደ ምሥራቅና ወደ ሰሜን የዘመተው ግዙፍ የወጣት ሠራዊት አላፈቀርምም አልተፈቀረምም እና ዘር አላፈራም? ከተምቤን ራስ አሉላን ተከትሎ ወደ መረብ-ምላሽ[iii] የዘመተው ዘማች በሞላ መች ተመለሰ? ብሂሉ "ሞኝ ያሸንፋል እንዴት ብሎ እምቢኝ ብሎ" ነውና አቶ ስብሓት ከእምዬ ምኒልክ ጋር ወደ ዓድዋ የዘመተው ሁሉ ተመልሶ ሄዷል አይሉም አልልም። ገዢ ነው፣ ታንክ ነው፣ ጄት ነው፣ ቦምብ ነው አይሉምም አልልም። ሊቀበሉ የማይፈልጉት ቢሆንም እውነቱን ግን ያጡታል ብዬ አልገምትም። ለምክንያት እኰ አይደለም ዓድዋ ከተማ ላይ የመሃል አገር ስም በርከት ብሎ የሚስተዋለው። የነ እንቶኔ የትውልድ ሃረግ ከዚህና ከዚያ መምዘዝ በድህረ-ተ.ሓ.ህ.ት. የተከሰተ ክስተት አይደለም። ኤርትራዊትዋ የሠራዬ ተወላጅ የአቶ መለስ እናት ወ/ሮ አለማሽ ወደ ትግራይ የመጡት፣ የዓድዋና የተምቤን ተወላጆቹ የአቶ ኢሳይያስ ወላጆች እነ አቶ አፈወርቅ አብርሃና የአክሱም ተወላጁ አቶ ወልደ-አብ ወልደ-ማርያም ወደ ሃማሴን የሄዱት በእነ አቶ ስብሓት ዘመን አይደለም። የገዢዎቻችን በሽታ ተጋብቶብኝ ዘር ቆጠራ መግባቴ አይደለም። አስረጅ ለማቅረብ ነው። ለእነርሱ ሳይሆን ለሦስተኛው ወገን።

የአንድነታችን፣ የትሥሥራችን ጉዳይ እነ አቶ ስብሓት ሊቀበሉት ስለማይፈልጉ ምንም ቢባሉና የፈለገው አስረጅ ቢቀርብላቸው አይቀበሉም እንጂ ብዙ አስረጅ ማቅረብ የማየስፈልገው ግልጽ ነገር ነው። አቶ አዲሱ ላቀረበላቸው ጥያቄ ቆጣ እያሉ ይመልሱ የነበሩትም ኃቁ እያፈጠጠባቸው ይመስለኛል። መቀሌ፣ ማይጨው፣ አዲግራት፣ ኲሓ፣ እንዳሥላሴ፣ ዓድዋ፣ እንትጮ፣ ውቅሮ፣ አሥመራ፣ ከረን፣ ምጽዋ፣ አሰብ፣ አዲ-ቀይሕ፣ ተሰነይ፣ ባሬንቱ፣ … ደብረ-ዘይት፣ ናዝሬት፣ ሰንዳፋ፣ ሓረር፣ አዋሽ አርባ፣ ኦጋዴን፣ ባሌ፣ … ወዘተ ሰፍሮ የኖረውና የሰለጠነው ሠራዊት እኰ ከዚያው አካባቢ ተመልምሎ የተቀጠረ የየአካባቢው ጐሳ ተወላጅ አልነበረም። ከሁሉም የአገሪቱ ማዓዝናት የተሰባሰበ ነው። የዛሬው ዓይነት የጐሳ ቆጠራ ብሂልና ደዌ ያኔ ቦታ አልነበረውም። ይህ ሁሉ ሠራዊት

ተ.ሓ.ህ.ት. ባይሆንም ሰው ነበር። ገዢዎቻችን ያሻቸውን ይበሉ ወልዷል፤ ተውልዷል። እነዚህን ከተማዎች ለአብነት መጥቀሴ ጉልህ ነቃሾች ስለሆኑ ነው። ይህ ሁሉ ኩነት ደግሞ ገሚሱ የገዢዎቻችን ድርጅት ከመቋቋሙ በፊት ብቻ ሳይሆን እነሱም ሳይፈጠሩ፤ ገሚሱ ደግሞ ድርጅታቸው ሳይፈጠር ነው። ሌላው ደግሞ ወደ ምኒልክ ግቢ ሊገቡ ቀርቶ መግባታቸው እንኳ ባላለሙበት ጊዜ የተከወነ ነው። ስለዚህ አቶ ስብሓት ከእሳቸው የሥልጣን ዘመን በፊት ኢትዮጵያውያን አንተዋወቅም ነበር ያሉት በፍጹም ስህተት ነው። የምንተዋወቅ ብቻ ሳይሆን በደምና በአጥንት የተሳሰርን፤ ቅድም አያቶቻችን በጋራ ወድቀውና ተነስተው፣ ቆስለውና ሞተው የገነቡልን የጋራ አገርና ታሪክ ያለን፣ አንዳችን ከአንዳችን በዘር ቆጠራ ልንለይ የማንችል ህዝብ ነን።

እንደሚያውቁት ግን ሊቀበሉት እንደማይፈልጉት ኃቅ ቢያንስ እላይ ከተጠቀሰው ዘመን ጀምሮ ያለው የአገራችን ተጨብጭ እውነታ ይህ ነው። እንኳንስ አማራና አፋር፣ ሶማሊና ትግራይ፣ ኦሮሞና ጉራጌ፣ ... ከፈረንጁ፣ ከአረቡ፣ ከህንዱ፣ ከቻይናው፣ ከኮርያው ጋርም ከተዋወቅን ቆይተናል'ኰ። የመገናኛው መንገድ ከአካባቢ የመራቅን ችግር ተረት-ተረት እያደረገው በመምጣቱ ትውውቃችንም፣ መዋለዳችንም እንዲሁ እያደገ ከመጣ ዘመናት አስቆጥሯል። የአቶ ስብሓት ባለቤት የጣልያን ትውልድ እንዳለባት፣ ወይዘሮ አዜብ አባታቸው የገዳሪፍ ተወልጅ ሱዳን ለመሆኑ የእነርሱ ሰዎች የሚናገሩት ውሸት ነው? ያም ተባለ ይህ ከጣሊያን ወረራ ማግስት ጀምሮ የዘመናችን ሥልጣኔ የፈጠረው ምቹ ሁኔታ ታክሎበት እንኳንስ በአገር ውስጥ ቀርቶ አህጉራትን አቋርጦ ርቆ መሰደድም የዓድዋ አዲ-አቡን ርቀት ያህል እየቀረበ መጥቷል። ያን ያህል ቀርቧል። ሰዋችን እንደ ጠበል የትም ተረጭቶ እየተማረም፣ ሠርቶ እየከበረም፣ ያላለለትም እየተዋረደ፤ ገሚሱም እንደወጣ እየቀረ መኖር ከጀመረ በጣም ቆይቷል። ይህ ዓለም-አቀፋዊ ክስተት ሲጀመር ደግም ተሓህት ሊፈጠር ቀርቶ አልታለመም ነበር። እነርሱስ ኰሮጃችሁን አንጠልጥለው ለልመና በየአህጉሩ ሲዞሩ ሲያስተናግዳቸው የነበረው ስደተኛ ኢትዮጵያዊ ከእነርሱ መሸፈት በፊት ተሰዶ የነበረ ጭምር አልነበረም እንዴ? ታዲያ ጣሊያን፣ አሜሪካ፣ ካናዳ፣ አውስትራሊያ፣ እንግሊዝና ጀርመን ቅርብ የሆነለት ህዝብ በምን ተአምር ሓረር፣ ጂማ፣ ለቀምት፣ አዲስ አበባና አሥመራ ራቀበትና እነርሱ መጥተው እስኪያስተዋውቁት ድረስ ሳይተዋወቅ ኖረ? እንደ ገዢዎቻችን የቸርቻሪ ዘመን የቻይና ተወላጅ በአንጐላ የጉሊት ነጋዴነትና በኢትዮጵያ በግምበኝነት የቀን ሠራተኛነት ሲርመሰመስ ባይታይም በጃንሆይ ዘመንስ በአገራችን የነበሩ የአሜሪካ፣ የህንድ፣ የእንግሊዝ፣ የግሪክ፣ የየመን፣... ሰዎች ቁጥር የሚናቅ እኰ አልነበረም። ታዲያ ይህንንም እነ አቶ ስብሓት የፈጠሩት ነው? እርግጥ ያኔና አሁን ልዩነት አለው፤ ያኔ በየሁለት ዓመቱ ፈቃዳቸው እያሳደሱ ይኖሩ የነበሩ ሲሆን አሁን ከኛ ይበልጥ ባለ ርስትና ጉልት እየሆኑ ከመሬታችን እየነቀሉን ነው። ሆን ተብሎ የቤት ሥራ እየተሰጠን ነው። መርዝ እየተተከለ ነው። ነገ አገራችን ለኛ ትሆን ለነሱ አንድዬ ይወቀው። እንግሊዞቹን ተከትሎ ወደ ኬኒያ የገባው ህንዳዊ ሥራ-ፈት አስካሪ'ኰ ወደአገሩ አልተመለሰም። የደቡብ አፍሪካው፣ የአንጐላው፣ ወዘተ እንዲሁ። ደግሞም እኰ አቶ መለስም በግልጽ ነግረዉናል፤[6] የምንሰማ ከሆነ። ከዚህ የበለጠ ሌላ አብነት ማምጣት አያስፈልግም። ገዢዎቻችን ነገራቸው ሁሉ ''አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም'' ሆነና ተቸገርን እንጂ ይህንን አያውቁትም ማለት አይደለም፤ ራሳቸውም እየነገሩን ነው። ያም ሆነ ይህ የህዝብ ዝውውር የነበረና ያለ ነው። ታዲያ አቶ ስብሓት ''እግዚአብሄር እንደፈጠርን ነው እኰ በክልላችን የነበርነው [ከ]*ፖሊስ መላክ፣ ወታደር መላክ፣ ጠቅላይ ገዢ መላክ* [በቀር]'' ብለው የገለጹት ስለማን ሲናገሩ ነው? በዚሁ ቃለ-ምልልስ እንኳን እራሳቸው ሳይቀሩ በአገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች እየተዘዋወሩ ለመሥራታቸው መስክረዋል። ከዚህም በላይ በአዲስ አበባ፣ በወልዲያ፣

6 Tamagn Beyene's presentation at the Washington D.C. ESAT fundraise event.

በጐንደር፣ በአሰብ፣ በሐረር፣ በአዋሳና በጅማ በተለያዩ የሥራ መስኮች ተሰማርቶ እንደማንኛውም ሌላው ወገኑ ጥሮ ግሮ ሲያድር የነበርው የሰሜኑ የአገራችን ክፍል ሰው በቀዬው ነው እንዴ የነበረው?ወይስ በአቶ ስብሓት ዓይን ሰው አይደለም? ዛሬስ ቢሆን መሄድ የፈለገው ነው እንጂ የሄደው መላው የትግራይ ህዝብ ወይም የሌላው አካባቢ ህዝብ እንዳለ ቀዬውን ለቆ ነቅሎ ሄዷል እንዴ? መቼም አሰብ ውስጥ ሠርቶ ሲኖር የነበረው ወሎዬና ትግራዋይ ሁሉ አገረ ገዥ ነበር ማለት አይቻልም።

*ለመሆኑ ጠቅላይ ገዢ ከመላክ በቀር* ያሉት እንዴት ነው? የትግራይ ገዥ የነበረው ማነው? እነ ልዑል ራስ መንገሻ ዮሐንስ፣ ልዑል ራስ ሥዩም መንገሻ፣ ልዑል ራስ መንገሻ ሥዩም አልነበሩም እንዴ? ባይሆኑ ኖሮስ? ትግራይ እኮ የኢትዮጵያ ክፍለ-ሃገር እንጂ ሌላ ራሱን የቻለ አገር አይደለም። ታዲያ ከሌላ አካባቢ የተላከ ኢትዮጵያዊስ ለምን አይሾምበትም? ብቁ ነው አይደለም ሥርዓቱ ይጨነቅበት። ኢትዮጵያዊ እስከሆነ ድረስ ግን አገሩ ነውና መብት አለው። በአንድ ወቅት አቶ መለስ ኢህአዴግ እስካመነበት ድረስ ማንንም ያገለግለኛል ብሎ ያመነበትን መሾም እንደሚችል እንደገለጹት ማለቴ ነው። የትግራይ-ትግርኝ ተወላጆቹ እነ አቶ ሰሎሞን አብራሃ (የአቶ ኢሳይያስ አፈ-ወርቅ አጐት) የወሎ እንደራሴ፣ ልጅ አበበ ረታ ሚንስትር፣ ወዘተ... የነበሩት፤ አቶ ስብሓት ሸዋ የሄዱትና በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች እየተዘዋወሩ የሰሩት በስደት ሄደው ነበር እንዴ? የጡት ልጃቸውስ ዋሽንግተን ወይም ደግሞ ለንደን መስሏቸው ነው ጀነራል ዊንጌትና አራት ኪሎ ግቢ የከረሙት? በቅድመ-ተ.ሓ.ህ.ት. ኢትዮጵያ ከቦታ ወደ ቦታ የሚላከው ወታደርና ገዢ ብቻ ነበር የሚለው አባባል በአቶ ስብሓት አፍ፣ በተሓህቶች አፍ ሲነገር በጣም ያሳፍራል። በአገሪቱ ሌላ ሰው ያልተፈጠረ ይመስል የትግራይና የቀረው የአገሪቱ ብሄራዊ ቁልፍ የሥልጣን ቦታዎች በዓድዋ ተወላጆች ጠቅጥቀው የያዙ፤ አገሪቱ ስንትና ስንት ንዋይ አፍስሳ ያፈራችው አገርና ህዝብ ያኰራ (ኰርያና ኰንጎን ልብ ይለዋል) ሞያተኛ ወታደርን በትነው በቀዬ ልጅነት ተጠራርተው ጀነራል ቅብርጥስ ተሰኝተው የተቀመጡ ሰዎች እኮ ናቸው እንዲህ የሚሉን። ከዘመነ መሳፍንት በኋላ የተካሄደው የዘመናዊቷ ኢትዮጵያ አገር የማቅናት ሂደት በምርጫ ሳጥን የድምጽ ቆጠራ አልተካሄደም። አፄ ቴዎድሮስም፣ አፄ ዮሃንስም፣ አፄ ምኒልክም፣ አፄ ኃይለ-ሥላሴም አምኖ የገበረውን እየሾሙ፣ ያመጸውን እየቀጡ ነው ግዛቶቻቸውን ያደላደሉት። ደርግም በጦርነት ኖሮ ያለፈው የሻዕቢያና ተ.ሓ.ህ.ት. ትንኰሳ አስገድዶትና ይህንን ሲያደርግ ነው። ተሓህቶችስ ብትሆኑ በአቅማችሁ የነገዋ ትግራይ-ትግርኝ ግዛት ለማስፋት ከጎንደርና ከወሎ በጉልበት መሬት ጐምዳችሁ ወስዳችሁ የለም እንዴ? ይህ ግን በኢትዮጵያችን ላይ ብቻ የተፈጸመ ተፍጻሜት አይደለም። ይህን አስመልክቶ የምናወጋው ነገር ዓለም በአንድ አዳራሽ ውስጥ ተቀምጦ መምከር ከጀመርበት በኋላ ባለው ዘመን ስለተፈጸመ ጉዳይ አይደለም። የአሜሪካ ጦር ብድግ ብሎ የሳዳም ሁሴንን መንግሥት እንደጨፈለቀበት ዓይነት የአንድ ጨርቃ ተፍጻሜትም አይደለም። እንዲያ ዓይነት አንድ ባዕድ አገር እምር ብሎ ተነስቶ ሌላን የባዕድ አገር የወረረበት ዓይነት ኩነትም አይደለም። እንዴት ነው ነገሩ?! የዛሬዋ ”ልዕለ-ኃያላን” አሜሪካስ እንደዘመናችን ፈሊጥ በጠረጴዛ ዙሪያ ድርድር ነው እንዴ የቀናቸው? እንግሊዝስ የቆመችው፣ ኢጣልያስ የቀናችው፣ ኰርያስ ለሁለት የተከፈለችው፣ ኤርትራስ የተገነጠለችው፣ ራሱ ኢህአዴግስ ቢሆን ያን ህዝብ ልቡን ነስቶና አምጾበት ተሸንፎና ሞቶ የጠበቀውን የኮ/ል መንግሥቱ መንግሥት ገለል አድርጐ አገሪቱን የተቆጣጠረው በጦር ኃይል አይደለም እንዴ? ለምንድን ነው በዓለማችን ሁሉም ማዓዝናት የተተገበረው መንግሥታትን የማቆም፣ አገሮችን የማቅናት የዚያን ዘመን ብልሃትና ዘይቤ ኢትዮጵያ ላይ ሲሆን ነውር፣ ወንጀል፣ የኃጢያቶች ሁሉ እናት የሚሆነው?

ገዢዎቻችን ለምን እንዲህ ዓይነት መረን የለቀቀ ጭፍን ፀረ-ታሪክና የአገሪቱ አንድነት ጥላቻ ሊያድርባቸው እንደቻለ ሊገባኝ አልቻለም። ይህንን አስመልክቶ ሌላ የተደበቀ የገዢዎቻችን ማንነት የምታውቁ ወንድሞች ፍንትው እንድታደርጉልን ከምጠይቅ በቀር በበኩሌ ምንም አመክንዮና መሰረት ላገኝለት አልቻልኩም። ያቺ እንዳትኖር ሊያደርጓት የሸፈቱባት አገር በዚያን ዘመን ከዚያ በላይ ምን ልታደርግላቸው ይገባት ነበር? እነርሱን ክሉልኝ ብላ፣ እነርሱን ፊት ነስታ በእነርሱ ደረጃ ለነበሩት ለሌሎች ያደረገችው የተለየ ነገር፣ የፈጸመችው አድልዎ ምን አለ? ምን ይህን ያህል ጥላቻ አሳድሮባቸው ለክህደትና ለጥፋትዋ እንዲሰሩ የሚያደርግ በደል በደለቻቸው? አቶ ስብሓት እየመረሩ ቸውም ቢሆን እንዳመኑበት በአገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች በአስተማሪነት ተሰምርተው ሰርተዋል (ከመሸፈታቸው በፊት የአክሱም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት-ቤት ርዕሰ-መምህር እንደነበሩ እዚያ የሥራ ቆይታ አድርጌ በነበረ ጊዜ ተረድቻለሁ። አቶ ስብሓት በዚያን ወቅት የዚያ ትምህርት-ቤት ተማሪ የነበረችን ከእርሳቸው የክህደት ዓላማ ጋር የማይስማማ አመለካከት የነበራት አንዲት ወጣትን በጩቤ ለማስገደላቸው በወቅቱ የገበያ ምስጢር ነበር)። ያንን ሞያ መረጡ፤ አግኝተው ሰሩበት። በእርግጥ፤ እንደ ዛሬው በጐሳ ላይ የተመሰረተ ያፈጠጠ፣ ያገጠጠ ሳይሆን በግለሰብ ቤተ-ሰባዊ ዝምድናና የዕድሞና ገረገር ትሥሥር ላይ የተመሰረተ በባለስልጣኖች ደረጃ የሚፈጸም አድልዎ ነበር። ዛሬም ያ ዓይነቱ ሙስና አለ፤ ወደፊትም ፈጽሞ ማስወገድ ቀላል አይሆንም። ይህ ግን አብረን እንዳንኖር ለመወሰን ምክንያት አይሆንም። ዛሬስ ቢሆን እነአቶ ስብሓት በሌላው ቀርቶ በአዲ-ዋዓሮና በሌላው የዓድዋ ተወላጅ መካከል እንኳ ሳይቀር አድልዎ ያደርጉ የለም እንዴ። በትላንቷ ኢትዮጵያ የወሎው ገዢ የአቶ ሰሎሞን አብራሃ የወንድም ልጅ ኢሳያስ አፈወርቅ፣ አስተማሪና ርዕሰ-መምህሩ ስብሓት ነጋ፣ የደላ ኑሮ የነበራቸው የአቶ ዜናዊ አስረስ ልጅ መለስ ዜናዊ፣ የተምቤኑ ፊውዳል የግራዝማች አብራሃ ልጅ ስዬ አብራሃ፣ የግራዝማች ኪዳነ ልጅ ካሳሁን ኪዳነ (የማነ ጀማይካ) ተቀማጥለው ሲማሩ፣ ሲሰሩና ሲኖሩ ዳቦ አሮበት እንደቅጠል የረገፈ የወሎ ህዝብም፣ ሌላ ሌላ ኢትዮጵያዊም ነበር እኮ። ይህንን ለመለወጥ መታገል የሚያኰራም የሚያስመሰግንም ነው። እነ የወሎው ዋለልኝ መኮንን፤ የትግራዮቹ ተወላጆቹ እነጥላሁን፣ እነ ተስፋዬ ደበሳይ፣ ጋይም (ገብረ-እግዚኣብሔር)፣… ይህንን ነው ያደረጉት። አገር ይፍረስ፤ ታሪክ ይካድ፣ ይንቋሸሽ ግን አላሉም።

ታሪክን መካድ አግባብ አይደለም። ለማንም አይጠቅምም። ዛሬ የምንፈልገውን ለመጠየቅ ትናንት ያልነበረን እንደነበረ አድርገን ማቅረብ አይገባም፤ አስፈላጊም አይደለም። አቶ ስብሓት የመላው ፀረ-ቅኝ ግዛት ትግል አርአያ፣ ኰርኳሪና መመኪያ የሆነው የዓድዋው ፀረ-ፋሺስት ኢጣሊያ ጦርነት ላይ የኢትዮጵያ ልጆች በጋራ ተሰልፈው፣ ተሰውተው፣ ቆስለው፣ ገድለው፣ ማርከው የተቀዳጁት የጋራ ድል ሲቀዳጁ አይተዋወቁም፣ አንተዋወቅም ነበር? በዚህ ጦርነት በጋራ የተሰለፉት ምኒልክና መንገሻ፣ አሉላና …፣ አውዓሎምና … ወዘተረፈ እንዲያው ድንገት ገበያ ወርደው ነው ነው የሚሉን? ዮሃንስ ጐንደር መተማ ዘምተው የተሰዉት የባዕድን አገር ለመጠበቅ ነው?

” ዐፄ ዮሐንስ ሞኝ ናቸው<br>
እኛም ሁላችን ናቅናቸው<br>
ንጉሥ ቢሏቸው በማኸሉ<br>
ወሰን ጠባቂ ልሁን አሉ<br>
በጐንደር መተኮስ፣ በደንቢያ መታረድ አዝኖ ዮሐንስ<br>
ደሙን አፈሰሰ እንደ ክርስቶስ<br>
እንዳያምረው ብሎ ድሃ ወዳጁን<br>
መተማ አፈሰሰው ዮሐንስ ጠጁን<br>
የጎንደር ሃይማኖት ቆማ ስታለቅስ አንገቱን ሰጠላት ዳግማይ ዮሐንስ<br>
እጅግ ደስ ይለኛል ያንተ ሥም ሲነሳ<br>
የቁና አፈር ንፋግ አንተ ነህ ወይ ካሳ? ”

ተብሎ የተገጠመላቸውም በማያውቁትና በማያውቅቸው ህዝብ ነውን?[7] አሉላ ኢጣሊያኖችን አይቀጡ ቅጣት እየቀጡና እያንቆራጠጡ ኤርትራን የጠበቅዋት፣ የምኒሊክን ጦር መርተው ወደ ደቡብ የዘመቱት በቅጥር የባዕድ ወታደርነት ነበር?[8] ሲዘምቱ ሳያውቁትና ወደማያውቁት አገር ነበር? በወቅቱ የነአቶ ስብሓት ሰልፍ ከጠላትጋር የነበረ በመሆኑ ማለታቸው ካልሆነ በቀር፤ ስንትና ስንት የትግራይ ልጆች ወደ ምሥርቅ ጦር ግንባር ዘምተው ከቀሩት የአገራቸው ልጆች ጐን ተሰልፈው የሶማሌን ወረራ የመከቱትና የተወረረው የአገራቸውን ክፍል ያስለቀቁት ለሽርሽር ሄደው ነው? አቶ ስብሓት፤ ይህ ሁሉ ሲፈጸም አንተዋወቅም ነበር ነው የሚሉን። ይህ ሁሉ እነ አቶ ስብሓት እንደሚቀባጥሩት ታሪክን ለማንሸውረር ከተቻልም እንደገና ለመጻፍ እንደሚሞክሩት ለአማራ ተብሎ የተደረገ አይደለም። ለአፄ ቴድሮስ፣ ለአፄ ዮሃንስ፣ ለአፄ ምኒሊክ፣ ለአፄ ኃይለ-ሥላሴ ወይም ለኰ/ል መንግሥቱ ተብሎ የተደረገም አይደለም። የኢትዮጵያ ህዝብ በተሓህቶች ዘመንም እኰ ከፋፋይ የፖለቲካ መርዝ ሳይበግረው በአንድነት ሆ ብሎ ባድሜ ላይ ገድል ፍጽሟል። ቁም ተባለና የሚገባው ድረስ ሳይዘልቅ ቀረ እንጂ ሌላም ሊሰራ ይችል ነበር። ይህን ያደረገው ግን ለተ.ሓ.ህ.ት. ብሎ አልነበረም፤ ለሚወዳት፣ ለሚንገበገብላት አገሩ ብሎ እንጂ። ያው አውቆ የተኛ ቢጠሩት አይሰማም ነውና እነ ስብሓት አሁን ይህን ያደረገው ስለተዋወቅን ነው ሊሉን መከጀላቸው አይቀርም። ለሌሎቹ እላይ ለጠቀስኳቸው ጉዳዮች ግን መልስ አይኖራቸውም።

እነ ስብሓት ነጋ የኢትዮጵያ አካል አይደለችም ብለው ተዋግተውና ፈርመው ያስገነጠሏት የኤርትራ ተወላጆች የሰሩት ኢትዮጵያዊ አገራዊ ገድልም ሌላ የዚህ አርቲ ቡርቲ ማርከሻ ማስረጃ ነው። ዘርዓይ ደረስ በጣሊያን አገር ለኢትዮጵያ ሲል የተዋደቀው ከባዕድ መካከል ለማማረጥ ሲል አልነበርም፤ በአገሩ በኢትዮጵያ መደፈር ተንገብግቦ እንጂ። በአፄ ኃይለ-ሥላሴ ዘመን ፋሺስት ጣሊያን ከርሱ ጋር ሆነው አገራቸው ኢትዮጵያን እንዲወጉ ያስታጠቃቸውን መሳሪ ይዘው በመክዳት ከሌሎቹ አርበኞች ወንድሞቻቸው ጋር ተቀላቅለው የታገሉትና እንደነ ኰ/ል ኃይለ አብ የመሳሰሉት የጥቁር አንበሳ ሠራዊት አባል የነበሩት ኤርትራዊያን ጀግኖች ለነስብሓት በውኑ ዓለም ያልነበሩ መናፍሳት ናቸው። ለእነ አቶ ስብሓት እነ ሞጐስ አስገኦም፣ አብራሃ ደቦጭ፣ የአገር ፍቅር ማህበር አባላት፣ ጀ/ል ገብረመድህን፣ ጀ/ል አርአያ፣ ኰ/ል ሰዓረ፣ ወዘተ... ። እነዚህ ሁሉ ከኢትዮጵያ ጋር አይተዋወቁም፤ ወይም የሚያደርጉትን አያውቁም። በሰሜን የአገራችን ልጆች ላይ ያተኰርኩት የሌላውን አካባቢ አርበኞቻችንን ዘንግቼ አይደለም። እንደነ አቶ ስብሓት የመሳሰሉ ፀረ-አንድነትና ከሃዲዎች በተፈጠሩበት አካባቢ እንኳ ሞግተው የማይረቱበት ኃቅ መሆኑን ለማሳየት ብዬ ነው። ሠፊው የትግራይ ህዝብ የተ.ሓ.ህ.ት. መሪዎችን እምነት፣ አቋምና ዓላማን አይጋራም። በአገሩ በኢትዮጵያ አንድነት ላይ ያለው አቋም መሰረተ ጽኑና ንቅንቅ የማይል ነው። የትግራይ ህዝብ ማንኛውም በአገሩ አንድነት ላይ የሚቃጣ ጥቃት ቢያንስ ቢያንስ ከሌላው ወገኑ በማይተናነስ ሁኔታ ሲመክት የኖረ ህዝብ ነው። ይህ ህዝብ ትግራይ ቀርቶ ኤርትራ እንዳትገነጠል ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍሏል። አገሩ በባዕዳን ወራሪዎች እንዳትወረርና እንዳትገዛ ሲታገል ኖሯል። በግብጽና በጣሊያን ወረራ ወቅት በሰሜን እና እሜን ምዕራብ፣ በሱዳን ድርቡሽ ወረራ ወቅት በጎጃም፣ በሶማሌ ወረራ ጊዜ በምስራቅ የአገሩን አንድነትና ሉዓላዊነት ለማስደፈር የከፈለው ዋጋ ማንም ሊክደው አይችልም። እስከ 1970 ዎቹ መጨረሻ ድረስ ተ.ሓ.ህ.ት.ን ገትሮ የያዘም በዋናነት ይህ ህዝብ ነበር። **የትግራይ ህዝብ ተ.ሓ.ህ.ት.ን አቋም የማይደግፍ ከሆነ እንዴት ታዲያ ተ.ሓ.ህ.ት. ሊያሸንፍ በቃ?**

---

7 ጎሩይ ወ. ሥላሴ (1910: 17)፤ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ (1938:84)

8 Erlich, H. (1996).

**በማን ታግዘውና ማንን አስታጥቀው የአሁኑ ገዥዎቻችን ለማሸነፍና ኤርትራንም ለማስገንጠል በቁ?** ይህ ራሱን የቻለ የውይይት ርዕስ ነው። ወደፊት እመለስበታለሁና ይቆየን።

ወደ ርዕሰ ጉዳዬ ልመለስ። በእርግጥ የፀረ-ኢትዮጵያዎች አባት አቶ ስብሐት ነጋ አንተዋወቅም ሲሉ አንድ ኃቅ አላቸው። በአንዲት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ማዕቀፍ ውስጥ የመኖር እምነትና ዓላማ ባለንና አንድነትዋ ላልቶ ተበጣጥሳ ትናንሽ መንግሥታት ሆና መመልከት በሚፈልጉ መካከል መተዋወቅ አልነበርም ብቻ ሳይሆን አሁንም የለም። የኢትዮጵያ ህዝብ የአቶ ስብሐት ነጋ ቡድን ወገን ከሆኑት የተ.ሓ.ህ.ት. መሪዎችና አጫፋሪዎች ጋር ትውውቅ የለውም። ወደፊትም አይኖረውም። አብሮም አይኖርም። በአካል እንጂ በመንፈስ አብረን እየኖርን አይደለም። እነሱም እየተዘጋጁና እንዲሆን እንቅልፍ አጥተው እየጣሩለት ያለውም እንዲያ እንዲሆን ነው። በመንግሥት ሥርዓት፣ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ የአመለካከትና የአቋም ልዩነት ቢኖር ነውር የለውም። ማንም ሰው ሥርዓትንና ገዢዎችን ቢኰንን፣ የተሻለ ነው የሚለውን የፖለቲካ ሥርዓት ለማምጣት ቢታገል፣ አለ የሚለውን በደል ለማጋለጥ ቢሠራ፣ ተገቢም መብትም ነው። ገዥዎች በፈጸሙት በደል ወይም ስህተት ሳቢያ አገርን ለመበተን መነሳት ግን በፍጹም ስህተት ነው፤ ወንጀል ነው፤ ዕብደት ነው። የተበላሸ ሥርዓትን ለውጦ መብትን የማስከበር ዓላማና አገርን የመገነጣጠል ዓላማ እንደ መንትያ አማራጮች መታሰብ የለባቸውም። በአገራችን መላ ህዝቧን የበደሉ፣ ያመቁ ገዥዎች ነበሩ። ዜጐችዋ በጋራ ተጨቁነዋል ተመዝብረዋል። ሆን ተብሎ ለብቻው ተለይቶ የተበደለ ህዝብ ግን አልነበረም። በአንድ አገር ውስጥ በአንድ የጊዜ ክልል ውስጥ በአንደኛው የአገሪቱ ክፍል ውስጥ የሚገኝን ህዝብ የሚያመቅ ኢ-ፍትሃዊ ሥርዓት በሌላኛው የአገሪቱ ክፍል ውስጥ ለሚገኘው ህዝብ ፍትሃዊ ሊሆን አይችልም። ለአንዳችን የጎረበጠ መንግሥትና አገዛዝ ለሌላችን ያገሪቱ ዜጎች አይደላንም። በትንሹም እንኳን ቢሆን የሚቀልልን አይሆንም። ተፈጥሮው እንዲያ እንዲሆን አይፈቅድለትም። አሜሪካዊው የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ማርቲን ሉተር በወቅቱ በአገራቸው የነበረው ሁኔታን አስመልክተው:-

> " I cannot sit idly by in Atlanta and not be concerned about what happens in Birmingham. **Injustice anywhere is a threat to justice everywhere.** We are caught in an inescapable network of mutuality, tied in a single garment of destiny. Whatever affects one directly, affects all indirectly. Never again can we afford to live with the narrow, provincial "outside agitator" idea." [9]

በማለት የገለጹት ይህንን ኃቅ ነው። ሆን ተብሎ ለብቻው ተለይቶ የተበደለ ህዝብ ነበረ እንኳን ቢባል በዳዩን በጋራ መንግሎ ለመጣል መታገል እንጂ ብድግ እያሉ "መሄዴ ነው፣ ያዙኝ ልቀቁኝ" መፍትሄ ሊሆን አይችልም። ኤርትራ ስለተገነጠለች የኤርትራ ህዝብ መብት ሲከበር አልታየም። ዴሞክራሲያዊ፣ ፍትሃዊ ሥርዓት እንጂ መለያየት የህዝብ ምርጫ አይደለም። ዜጐችዋ ማበር እንጂ መበታተን ትሩፋትና ጥንካሬ አያስገኝላቸውም። ለአንድነት ሲባል መረገጥ አይገባም። አማራጩ ግን ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማስፍን በጋራ መታገል እንጂ ብተና አይደለም። የአውሮጳውያን ጥረት ለህብረት ለዚህ አብነት አድርጐ ማቅረብ ይቻላል።

ይህንን እውነታ ለአንዳንድ የምዕራብ ትግራይ ወንድሞቻችን ለምን እንደተሰወረባችው መረዳት በጣም የከበደ ነገር ነው። እዚያ ምዕራብ ትግራይ ጥቂቶቹን እንዲያ አድርጐ የሚያሳብድ የዕብደት ልክፍት አለ ይሆን?! ወልደ-አብ ወልደ-ማርያም(አክሱም)፣ ኢሳያስ አፈወርቅ (ዓድዋና ተምቤን)፣ ሙሴ ተኽለ (አክሱም)፤ ስብሐት ነጋ፣ አባይ ፀሃዬና መለስ ዜናዊን (ዓድዋ) በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ ለኤርትራ መገንጠል የሰሩና ያስገነጠሉ ናቸው።

---

9 Martin Luther King, Jr (1992).

ከዚህም ሌላ ስብሓት ነጋ፣ አባይ ፀሃዬና መለስ ዜናዊ የትግራይን ህዝብ መብት በኢትዮጵያ ማዕቀፍ ውስጥ ለማስከበር ሳይሆን ትግራይን ለማስገንጠል ተነስተው በወቅቱ በአብዛኛው የድርጅታቸው አባል ተቃውሞ ከሸፎባቸዋል። ነገርግን ይህንን አጀንዳቸውን በይደር አቆይተዉት የነበረ እንጂ ፈጽመው ያልሻሩት ስለሆነ ዛሬ ለወትሮው የኢትዮጵያን አንድነት ለማስከበር ይመከርበት በነበረው የምዬ ምኒልክ ቤተ-መንግሥት ውስጥ መሽገው ለዓላማው መሳካት በመሥራት ላይ ናቸው። የቅርቡ የአቶ ስብሓት እክሱም ለዓጋመና ለተምቤን ምኑም አይደለም የድፍረት አነጋገር ምዕራብ ትግራይን (አክሱም፣ ሽሬ፣ ዓድዋና ወልቃይት ጠገዴን)ይዘው ከኤርትራ ጋር የመቀላቀል ዓላማቸውን የሚቃወመውን የቀሩት የአምስቱ አውራጃዎች ህዝብን ከጉዳዩ ጋር የማለማመድ ጅማሮ ሊሆን ይችላል (እላይ እንደገለጽኩት በሌላ ጊዜ እመለስበታለሁ)።

አቶ ስብሓት በዚሁ ቃለ-ምልልሳቸው አንድነቱ አሁን እየመጣ ነው ብለውናል። ይህንን አባባላቸው ብዙ የትግራይ ከፍለ-ሃገር ተወላጅ ወንድሞቻችን ሲጋሩት ይሰማል፤ በየዋህነትም ሆነ በገዢው ቡድን ጋሻ-ጃግሬነታቸው። የጋራ እሴቶቻችን መንምነው እንዲበጠሱ እየተደረገ፣ የጋራ አገራችን በትናንሽ የጐሳ መንግሥታት እንድትተካ የክልል መንግሥታት እየተበጀልን፣ የጋራ መለያችን የሆነው ሰደቅ-ዓላማችን (በቴድሮስም፣ በዮውሓንስም፣ በሚኒልክም፣ በሃይለ-ስላሴም፣ በደርግም የነበረው) የሚተካና የበለጠ በጐሰኝነት መንፈስ የምናመልክበት ብጥቅጣቂ በየመንደሩ እየታደለን፣ በተኪው ትውልድ አዕምሮ ውስጥ ነገ አንድነታችንን የሚገድል መርዝ እየተተከለ፣ ወዘተ ወዘተ እንዴት ሆኖ ነው አንድነት የሚመጣው?! ገዢዎቻችን ዛሬ የህዝቡን ቁርኝት እንዳይጠገን አድርገው እየበጣጠሱት ነው። የሚያስተሳስሩንን ኅብረ-ብሄራዊ ተቋማት እየፈራረሱና እየተገደሉ ነው። የጋራ መለያችን የሆነው ባንዴራችን በጐሳ መለያ ምልክቶች እየተተካ ነው። ባለፋት መንግሥታት (በዐፄ ዮሐንስ ጭምር) የጋራ መግባቢያ ሆኖ ስንገለገልበት የነበርው የጋራ ቋንቋ በሂደት እንዲከስም እየተደረገ ነው። የጐሳ መንግሥታትና የጐሳ ምክር-ቤቶች እየተበጁልን ነው።በአጭሩ በአገሪቱ የሚገኙ የተለያዩ ጐሳዎች ነገ ራሳቸውን የቻሉ መንግሥታት እንዲሆኑ ሊያበቃቸው የሚይስችል ሥራ እየተሰራ ነው። አንድነቱ በየት በኩል ነው እየመጣ ያለው? ቁጥራቸው የማይናቅ የኤርትራ ወድሞቻችንን በነፃ መውጣት ሥም በመገንጠል ስሜት እንዲሰክሩ የተደረጉት ባዕዳን ለመለያያ ብለው በፈጠሩት የፌደሬሽን መለያና ክልል በማደናገር ለመሆኑ አቶ ስብሓትም ሆኑ ሌሎች የሚስቱት አይመስለኝም። እስከዛሬ ድረስ ይህ ስካር ያልለቀቃቸው ወንድሞቻችን ቁጥር ቀላል አይደለም። ነገ ይህ በቀረው የአገራችን ክፍል እንዳይደገም የሚያደርግ ምንም ተዓምር የለም። ይህንን ሲደረግ ዝም ብለው የሚመለከቱ ጊዜው ፈቅዶላቸው ዕውቀቱም፣ ገንዘቡም፣ ስልጣኑም ሆነ በዚያ ዙሪያ የመንጠልጠሉ ዕድል ያገኙ ሰዎች ነገ ተጠያቂነት አለባቸው። ሁሌም አገር የሚጠፋው፣ ህዝብ የሚታመሰው በጥቂት ባለሥልጣናት ክፉ ሥራ ብቻ አይደለም፤ በአጫፋሪዎቻቸውና የመከላከል አቅም እያላቸው ዝም ብለው በሚመለከትዋቸውም ጭምር ነው። ዛሬ ለመናኛ ፍርፋሪ ብለው ለመጣው ሁሉ ሰጋጅ የሆኑት ምሁራንና ከበርቴዎች ነገ ከህዝቡ የሚደርስባቸውን ቅጣት አሰላስለው ሳይመሽ ሊመክሩበት ይገባል። እነሱም ሆኑ ተተኪዎቻቸው በሰላም መኖር የሚችሉት ሁሌም ሰልፋቸው ከህዝብ ወገን ሲሆን ብቻ ነው። በጣሊያን ወረራ ዘመን ከወራሪው የጣሊያን ሠራዊትና ከባንዳው ጋር ሲያሸቃብጡ የነበሩትን ለማስጠንቀቅ ”ዓርኰም ይሄድና፣ ሶሊዲውም ያልቅና ያስተዛዝበናል ይቺ ቀን ታልፍና” ተብሎ የተገጠመው ዛሬም ለወደፊትም የሚሰራ ምክርና ማስጠንቀቂያ ነው።

በተረፈ አበው እንደሚሉት ”ርኩስ ከሚበላህ በልተኸው ተባረክ” ማለትን መዘንጋት አይገባም።

**ሰሎሞን ወልደ፡አብ**

## ምንጮች


ህ.ወ.ሓ.ት. (1979). የኤርትራ ህዝብ ትግል ከየት ወዴት! (ግምገማ). በአብራሃም ያይህ (1992). *የኤርትራ ህዝብ ትግል ከየት ወዴት! (ግምገማ) ትችት።* ዋሽንግተን ዲሲ፣ ፈጣን ግራፊክስ ኮሮፖሮሽን።

ኅሩይ ወ. ሥላሴ (ብላቴን ጌታ) (1910)። *ኢትዮጵያ-መተማ* የዐፄ ዮሐንስ ታሪክ። አዲስ አበባ ፤ ኢትዮጵያ ማ/ቤት

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ(1938)፤ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ*፤ 4ኛ መጽሐፍ፣ አዲስ አበባ፤ መርሐ ጥበብ ማተሚያ ቤት። በተክለ ጻድቅ መኩሪያ (1982)፡ *ዐፄ ዮሐንስ እና የኢትዮጵያ አንድነት።* አዲስ አበባ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።

Berhe, Aregawi. (2009). *A political history of the Tigray People's Liberation Front (1975-1991): revolt, ideology and mobilisation in Ethiopia.* (1st ed.) Los Angeles, CA: Tsehai Publishers & Distributors.

Berhe, Kahsay (2005). *Ethiopia: Democratization and Unity. The role of the Tigray People's Liberation Front.* Münster: Verlagshaus Monsenstein und Vannerdat.

Erlich, H. (1996). *Ras Alula and the scramble for Africa: a political biography: Ethiopia and Eritrea 1875-1897.* Lawrenceville, NJ: Red Sea Press.

Martin Luther King, Jr (1992). *Letter from Birmingham Jail, April 16, 1963*. Retrieved 01 June 2012, from www.africa.upenn.edu/Articles_Gen/Letter=Birmingham. html

ስብሓት ነጋ (2004)፤ "የእኛ ሀገር ተቃዋሚ ፓርቲዎች የተቆጣ ህዝብ የሚወክሉ ሳይሆን በግላቸው የተቆጡ ሰዎች ይመስሉኛል።" ቃለ-ምልልስ ከሰንደቅ ጋዜጣ ጋር፣ ሰንደቅ፣ 7ኛ ዓመት፣ ቁጥር 337፣ የካቲት 14/2004። በዘ ሐበሻ፤ www.zehabesha.com/?p=4630

Tamagn Beyene's presentation at the Washington D.C. ESAT fundraise event. Www.youtube.com/watch?v=n6qSul13Ikw&feature=related


### የግርጌ ማስታወሻ

i የተሓህት መሪዎች የሚጠሩት በእውነተኛ ስማቸው አይደለም፤ በሽፍትነት ስማቸው እንጂ። በበረሃ ዘመናቸው ማንነታቸውን ለመደበቅ ብለው ተጠቅመውበት እንደሆነ ከተማ ሲገቡ በእውነተኛ ስማቸው ሊጠሩ፤ ወይም ደግሞ በአገሪቱ ህግ መሰረት ሊያቀይሩ ሲገባ ከህግ በላይ ናቸውና አልተጨነቁበትም። ከማን ለመደበቅ የበርሃ ስም እንዳስፈለጋቸውም እግዚአብሔር ይወቀው። ደርግ እንደሆነ ስለማንነታቸውና ዘር ማንዘራቸው አብጠርጥሮ ያውቅ ነበር።

ii እንደርታ በቅድመ-ተሓህት ኢትዮጵያ ከነበሩት 8 አውራጃዎች አንዱ ነው። ይህ አውራጃ በወቅቱ በቆዳ ስፋቱ ከሁሉም አውራጃዎች የተለቀ ነበር።

iii ወራሪው የኢጣሊያ ፋሺስት መንግሥት እንደ አውሮጳዊያን አቆጣጠር ጃንዋሪ 1 ቀን 1890 ኤርትራ ብሎ ያጠመቃት የኢትዮጵያ ታሪክ እምብርት አካለ-ምድር።

i

ii

iii